# የእንስሳት መድኃኒትና ሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ችርቻሮ ንግድ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 14/2012

Veterinary Medicine and Medical Equipment Retail Establishment Qualification Certificate Issuance Guidelines (Directive 14/2012)

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርናጥጥር ባለስልጣን
Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority

ነሀሴ 7፥ 2012

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

መግቢያ ........ 1
ክፍል አንድ
አጠቃላይ
አጭር ርዕስ ........ 2
ትርጓሜ ........ 2
ክፍል ሁለት
የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ እና ተቋማት
የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ........3
የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት........ 4
የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች ዲዛይን፤አሠራርና የአካባቢ ሁኔታ 4
ክፍል ሶስት
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ
አስፈጻሚ አካል ........ 5
ኮሚቴ ስለማቋቋም
የኮሚቴው አባላት ........ 5
የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት ........ 5
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታ
የእንስሳት መድኃኒት መደብር ........ 6
የእንስሳት መድኃኒት መደብር ሊያሟላቸው ስለሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች. 7
የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ........ 8
የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ሊያሟላቸዉ ስለሚገቡ ሁኔታዎች ........ 9
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት........ 9
ክፍል አራት
አጠቃላይ ድንጋጌዎች
የአገልግሎት ክፍያ ........ 11
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚታይበት ሥፍራ ስለማኖር ........ 11
የእንስሳት መድኃኒት ማሸጊያና ገላጭ ጽሁፍ........ 11

መድኃኒት ግዥና ሽያጭ ........ 11
ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ........ 12
የደንብ ልብስ ........ 12
የሥራ ሰዓት ........ 12
መድኃኒት አያያዝ ........ 12
ሪከርድ አያያዝና ሪፖርት አደራረግ ........ 12
ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ........ 13
ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ........ 13
ዝዉዉር ወይም ቦታ ለዉጥ ........ 14
የባለሙያ ለዉጥ ........ 14
የተከለከሉ ተግባራት ........ 14
ግዴታ ........ 15
ክፍል አምስት
አስተዳደራዊ እርምጃዎች
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማገድ ........ 15
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መሠረዝ ........ 16
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መመለስ ........ 16
መመሪያዉን ስለማሻሻል ........ 17
የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች ........ 17
መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ ........ 17
ዕዝል ........ 18

# መግቢያ

የተሟላ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ፈዋሽነታቸው፣ ደህንነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶች በማያቋርጥ ሁኔታ መገኘትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ወሳኝነት አለው፡፡ መንግሥት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከልና ለማከም የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች በአግባቡ እንዲቀርቡ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ የእንስሳት መድኃኒቶች ከእንስሳት ጤንነትና ምርታማነት ጋር በቀጥታ የተሳሰሩ፣ በተፈጥሮአቸው የመርዛማነት ባሕርይ ያላቸውና ከጥሬ ዕቃዎች ዝግጅት ጀምሮ በምርት፣ በክምችት አያያዝ፣ በማከፋፈልና በችርቻሮ ሂደት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካልተደረገበት የጥራት ደረጃቸው፣ የፈዋሽነታቸውና ደህንነታቸው ባህርይን ሊያጡ ወይም ሊለወጡ ስለሚችሉ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም እስከ ማሳጣት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

ስለሆነም የእንስሳት መድኃኒት ዕደላ መካሄድ ያለበት በሙያው ጠለቅ ያለ ዕውቀትና አግባብ ባለው ባለሙያ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ጥራታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቁ የእንስሳት መድኃኒቶች ለተገልጋዩ ለማዳረስ ለክምችት፣ አያያዝና ዕደላ አመቺ የሆነና የተሟላ ተቋም መኖር አለበት፡፡

በመሆኑም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት የእንስሳት መድኃኒቶች ዕደላ ተግባር መመዘኛዎችና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት በተገቢው መንገድ እንዲከናወን ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ችርቻሮ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 14/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀጽ 2 ስር ለተቀመጡ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ:

1. "የእንስሳት መድኃኒት" ማለት የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለማከም ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የውስጥና የውጭ ጥገኞችንና በሽታ አስተላላፊ ተባዮችን ማከሚያ ውህዶችን፣ ባዮሎጂካል ውጤቶችን፣ የሳኒተሪ መገልገያዎችንና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎችን ያካትታል፤
2. " የእንስሳት ሕክምና መሣሪያ" ማለት የእንስሳት በሽታን ለመመርመር ወይም ለማከም ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያ ሲሆን የዉጭ ጥገኛ መርጫ መሣሪያዎች፤ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ጥገና፣ የማዋለጃ፣ የሰዉ ሠራሽ ማራቢያና የማኮላሻ መሣሪያዎችንም ያካትታል፤
3. "የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም" ማለት የእንስሳት መድኃኒቶችን ከጅምላ ሻጭ ገዝቶ ለተጠቃሚ የሚሸጥ የእንስሳት መድኃኒት መደብር ወይም የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ሲሆን ጅምላ ሻጭ ወይም አምራች ወይም አስመጪ የእንስሳት መድኃኒቶችን ለተጠቃሚ ሲሸጥ የችርቻሮ ንግድ ውስጥ እንደተሳተፈ ይቆጠራል፡፡ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም የእንስሳት መድኃኒቶችን ለሌላ የችርቻሮ ንግድ ተቋም ሲሸጥ በጅምላ ንግድ ውስጥ እንደተሳተፈ ይቆጠራል፡፡
4. "የእንስሳት መድኃኒት መደብር" ማለት አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ፈቃድ በተሰጠው የእንስሳት ሐኪም ወይም የእንስሳት ጤና ፋርማሲስት ወይም የእንስሳት ህክምና

ቢ.ቪ.ኤስ.ሲ ወይም ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ ባለው ባለሙያ የሚመራ የችርቻሮ ተቋም ነው፤

5. "የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት" ማለት አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ፈቃድ በተሰጠው የእንስሳት ጤና ደረጃ IV ባለሙያ ወይም ረዳት የእንስሳት ሐኪም ወይም የእንስሳት ጤና ድራጊስት ወይም የእንስሳት ጤና ፋርማሲ ቴክኒሺያን ሆነው የብቃት ምዘና ወስደው ያለፉ ወይም ከዚያ በላይ የሙያ ደረጃ ባለው ባለሙያ የሚመራ የችርቻሮ ንግድ ተቋም ነው፤
6. "አግባብ ያለው አካል" ማለት የእንስሳት መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ተግባራትን የማከናወን ስልጣን የተሰጠው የክልል መስተዳድር ግብርና ቢሮዎች ወይም የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲዎች ማለት ነው፤
7. "ባለስልጣን" ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው::
8. "እገዳ" ማለት ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ባለስልጣኑ ያወጣዉን የቁጥጥር መመሪያ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት ከሶስት ወር እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ ስራውን እንዲያቋርጥ የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤
9. "ስረዛ" ማለት ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም ባለስልጣኑ ያወጣዉን የቁጥጥር መመሪያ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት ከሁለት አመት ለማያንስ ጊዜ ስራውን እንዳይሰራ የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤
10. "ኢንስፔክሽን" ማለት አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ለሚሰሩ ተቋማት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ወይም ለማደስ ወይም የቁጥጥር ስራ ለመስራት ተቋሙ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘቱን ለማረጋገጥ በባለሙያዎች ምልከታ ማድረግ ነው::

## ክፍል ሁለት

### የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ እና ተቋማት

3. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ

ማንኛውም ሰው አግባብ ካለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል ከተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተግባር ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

## 4. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት

1. የእንስሳት መድኃኒት መደብር ሊቋቋም የሚችለው አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሰጠው የእንስሳት ሐኪም ወይም በእንስሳት ህክምና ቢ.ቪ.ኤስ.ሲ ወይም ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ ባለው ባለሙያ የሚመራ የእንስሳት ጤና ክሊኒክ በአካባቢው መኖሩ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡
2. የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ሊቋቋም የሚችለው አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሰጠው የእንስሳት ጤና ደረጃ IV ባለሙያ ወይም በረዳት የእንስሳት ሐኪም ወይም ከዚያ በላይ የሙያ ደረጃ ባለው ባለሙያ የሚመራ የእንስሳት ጤና ክሊኒክ ወይም የእንስሳት ጤና ኬላ በአካባቢው መኖሩ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 5. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት ዲዛይን፣ አሠራርና የአካባቢ ሁኔታ

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት ክፍሎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መሠረት መዘጋጀት አለባቸው፡፡
   ሀ. ወለሉ ከሲሚንቶ ወይም ከጣውላ ወይም ከሸክላ የተሰራ፣
   ለ. ግድግዳው ሊታጠብ በሚችል ቀለም የተቀባ፣
   ሐ. በቂ ብርሃን ሊያስገባ የሚችልና በቂ የአየር ዝውውር ያለው፣
   መ. ጣራው ሙቀትን የሚቀንስ ኮርኒስ ያለው እንዲሁም
   ሠ. የግድግዳው ቁመት ከ2.8 ሜትር የማያንስ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት የአካባቢ ሁኔታ በሚመለከተው መልኩ መሆን አለበት፡፡
   ሀ. ድርጅቱ የሚቋቋምበት አካባቢ ንጽሕናው የተጠበቀ፣ ከሕዝብ ሽንት ቤትና ቆሻሻ ከሚከማችበት አካባቢ ቢያንስ 100 ሜትር የራቀ፣
   ለ. የድርጅቱ ማደያና ማከማቻ ክፍሎች ጎርፍ የማያስገቡ እና የመድኃኒቱን ጥራት ሊለዉጡ ከሚችሉ ሌሎች ማናቸውም ነገሮች የፀዳ አካባቢ፣

ሐ. የተቋሙ ስም በአማርኛ ወይም በአካባቢው ቋንቋ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ወይም በተቋሙ የመግቢያው በር ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

# የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ

## 6. አስፈጻሚ አካል

የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድሮች ጨምሮ በክልል ግብርና ቢሮዎች ወይም የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲዎች ይሆናል፡፡

### 1 ኮሚቴ ስለማቋቋም

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥን ለማቀላጠፍና ፍትሐዊነቱንም ለማረጋገጥ እንዲቻል ስለሚቋቋም ኮሚቴ፤

ሀ. የኮሚቴው አባላት

1. አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የእንስሳት ጤና ኃላፊ ወይም የሥራ ሂደት ባለቤት..............................................................................ሰብሳቢ
2. አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ሥራ ሂደት ሥር ካሉት አንድ የእንስሳት ሀኪም..............................................................................ፀሐፊ
3. አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ሥራ ሂደት ሥር ካሉት አንድ የእንስሳት ጤና ባለሙያ...........................................................አባል

ለ. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማትና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄዎችን ይቀበላል፣ መረጃዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን እንዲከናወን ይወስናል፣ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ጥያቄ ያቀረቡት የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት በመመሪያው የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ያካሂዳል፤

3. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት ኢንስፔክሽን ሪፖርት ወይም የባለሙያ ብቃት መረጃ ይገመግማል፤ በግምገማ ውጤት መሰረት አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ አዲስ የሙያ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ፣ እንዲታደስ፣ እንዲከለከል፣ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ያደርጋል፤
4. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት ተገቢውን የብቃት መመዘኛ ማሟላታቸውንና ባለሙያዎች የሙያው ስነ-ምግባር በሚያዘው መሠረት ሕግና ደንብን ተከትለው የሚሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ድንገተኛ ኢንስፔክሽን ያካሂዳል፤
5. ጉድለቶች ሲኖሩም በመመሪያው መሰረት የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤
6. ፈቃድ የተሰጣቸው እና ፈቃዳቸው የታገደ ወይም የተሰረዘ ተቋማት ወይም ባለሙያዎች ለባለስልጣኑና ሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በጊዜው ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታ

### 1. የእንስሳት መድኃኒት መደብር

የእንስሳት መድኃኒት መደብር ለማቋቋምና ሥራውን ለመምራት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 የተጠ ቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ባለሙያ የሚከተሉት መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

ሀ. በእንስሳት ሐኪምነት ወይም በእንስሳት ጤና ፋርማሲስት ወይም በእንስሳት ሕክምና ቢ.ቪ.ኤስ.ሲ ወይም ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ የተመረቀ ሆኖ ዜሮ ዓመትና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው መሆኑ አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ሲረጋገጥ፣

ለ. ባለሙያው በሙያው ተሰማርቶ እንዳይሰራ በሕግ ያልተከለከለ መሆኑን ሲረጋገጥ፣

ሐ. የሙያ ግዴታውን ለመወጣት የማያስችል የአእምሮ ሕመም ወይም ሌሎች ከሙያው ጋር የተያያዙ ችግሮች የሌሉበት መሆኑን ሲታወቅ፣

መ. የአልኮል መጠጥ ወይም የናርኮቲክና የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ሱሰኛ ያልሆነ፡፡

ሠ. ባለሙያው የስራ ልምድ ያለው ከሆነ ይሰራበት ከነበረው መሥሪያ ቤት የሥራ መልቀቂያ ሲያቀርብ ወይም ከሌላ ክልል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ አውጥቶ በዘርፉ ሲሰራ ከነበረ ምስክር ወረቀቱን የመለሰ መሆኑን ከክልሉ መስተዳድር ወይም አግባብ ካለው አካል ማስረጃ ሲያቀርብ ወይም በረዳትነት በዘርፉ ይሰራ ከነበረ ከተሰማራበት ተቋም ማስረጃ ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

## 2. የእንስሳት መድኃኒት መደብር ሊያሟላቸዉ ስለሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት መደብር እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የተሟላ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌፎንና የውሃ አገልግሎቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡
2. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት መደብር በውስጡ፣
   ሀ. የመድኃኒት ማከማቻ ክፍል፣
   ለ. የመድኃኒት ማደያ ክፍል፣
   ሐ. የጽህፈት ሥራ ለማካሄድ የሚያስችል ቦታና የልብስ መቀየሪያ፣
   መ. እንደ አካባቢዉ ሁኔታ የመፀዳጃ ክፍል ሊኖረው ይገባል፡፡
3. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት መደብር ማደያ ክፍል፣
   ሀ. ስፋቱ ቢያንስ ሃያ (20) ካሬ ሜትር ሆኖ የአነስተኛው ጎን ርዝመት ከአራት (4) ሜትር ማነስ የለበትም፡፡
   ለ. የመድሃኒት ማደያ ክፍል በውስጡ በቂ የመድኃኒት መደርደሪያዎች፣ ባንኮኒ፣ የክፍሉ ሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር፣ የእሳት አደጋ መከላከያ (ማጥፊያ) መሣሪያ ሊኖረዉ ይገባል፡፡
4. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት መደብር ማከማቻ ክፍል፣
   ሀ. ስፋቱ ቢያንስ አሥራ ሁለት (12) ካሬ ሜትር ሆኖ የአነስተኛ ጎኑ ርዝመት ከሦስት (3) ሜትር ማነስ የለበትም፡፡
   ለ. የማከማቻ ክፍሉ በውስጡ በቂ የመድኃኒት መደርደሪያዎች፣ ቅዝቃዜ ለሚሹ መድኃኒቶች ማቀዝቀዣ ከነሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር፣ የክፍሉ ሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር
   ሐ. ከፍተኛ ሙቀት ባሉባቸው አካባቢዎች መድኃኒቶች ያሉባቸውን ክፍሎች በሚያዳርስ ሁኔታ እንደሚሰራ የተረጋገጠ ኤር ኮንዲሽነር ወይም ቬንትሌተር ፣
   መ. የውጭ ጥገኛ፣ መርዛማና ተቀጣጣይ የሆኑ መድኃኒቶች ሊቀመጡበት የሚችል የተለየ ቦታ ሊኖሩት ይገባል፡፡

5. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ መደብር የጽህፈት ሥራ የሚካሄድበትና ልብስ የሚቀየርበት ተስማሚ ተብሎ የተመደበ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡
6. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ መደብር ለተግባር ማከናወኛ የሚሆን፣
   ሀ. ጠረጴዛ ቢያንስ አራት ተሳቢ ያለው፣
   ለ. ቢያንስ ሁለት ወንበሮች፣
   ሐ. ባለ ቁልፍ ፋይል ካቢኔት፣
   መ. እስቶክ ካርድና የልብስ መስቀያ ሊኖሩት ይገባል፡፡
7. የእንስሳት መድኃኒት መደብር መፀዳጃ ክፍሉ የውሃ አገልግሎትና የእጅ መታጠቢያ ሲንክ ያለው መሆን አለበት፡፡

## 3. የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት

የእንስሳት ገጠር መድኃኒት መደብር ለማቋቋምና ሥራውን ለመምራት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ባለሙያ የሚከተሉት መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

ሀ. በረዳት እንስሳት ሐኪምነት ወይም በእንስሳት ጤና ደረጃ IV ባለሙያ ወይም በእንስሳት ጤና ድራጊስት ወይም በእንስሳት ጤና ፋርማሲ ቴክኒሽያን የተመረቀ ሆኖ የብቃት ምዘና ወስደው ያለፉና ዜሮ ዓመትና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው መሆኑ አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ሲረጋገጥ፣

ለ. በዚህ ንኡስ አንቀፅ ተራ ቁጥር ሀ ላይ የተጠቀሰው የሙያ ደረጃ እንደተጠ በቀ ሆኖ ከዚያ በላይ የሙያ ደረጃ ያላቸው ባለሙያዎችም ማመልከት ይችላሉ፡፡

ሐ. ባለሙያው በሙያው ተሰማርቶ እንዳይሰራ በሕግ ያልተከለከለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ. የሙያ ግዴታውን ለመወጣት የማያስችል የአእምሮ ሕመም ወይም ሌሎች ከሙያው ጋር የተያያዙ ችግሮች የሌሉበት መሆኑን ሲታወቅ፣

ሠ. የአልኮል መጠጥ፣ የናርኮቲክና የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ሱሰኛ ያልሆነ፣

ረ. ባለሙያው የስራ ልምድ ያለው ከሆነ ይሰራበት ከነበረው መሥሪያ ቤት የሥራ መልቀቂያ ሲያቀርብ ወይም በሌላ ክልል ወይም አካባቢ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ አውጥቶ በዘርፉ ይሰራ ከነበረ የምስክር ወረቀቱን የመለሰ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ አግባብ ካለው አካል ማስረጃ

ሲያቀርብ ወይም በረዳትነት በዘርፉ ይሰራ ከነበረ ከተሰማራበት ተቋም ማስረጃ ሲያቀርብ፣

## 4. የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ሊያሟላቸዉ ስለሚገቡ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት እንደየአካባቢው ሁኔታ የተሟላ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌፎንና የውሃ አገልግሎቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡
2. ማንኛውም የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት በውስጡ፡-
   ሀ. የመድኃኒት ማደያ ክፍል፣
   ለ. የመድኃኒት ማከማቻ ክፍል፣
   ሐ. እንደ አካባቢዉ ሁኔታ የመፀዳጃ ክፍል ሊኖረው ይገባል፡፡
3. ማንኛውም የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ማደያ ክፍል፡-
   ሀ. ስፋት ቢያንስ አሥራ አምስት (15) ካሬ ሜትር ሆኖ የአነስተኛው ጎን ርዝመት ቢያንስ ሦስት (3) ሜትር መሆን አለበት፡፡
   ለ. በውስጡ በቂ የመድኃኒት መደርደሪያዎች፣ የግድግዳ ሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር፣ የእሳት መከላከያ ወይም ማጥፊያ መሣሪያ፣ የጽህፈት ሥራ ለማካሄድ የሚያስችል ቦታና የልብስ መቀየሪያ ሊኖሩት ይገባል፡፡
4. ማንኛውም የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ማከማቻ ክፍል፡-
   ሀ. ስፋቱ ቢያንስ ዘጠኝ (9) ካሬ ሜትር ሆኖ የአነስተኛ ጎኑ ርዝመት ከሁለት ተኩል (2.5) ሜትር ማነስ የለበትም፡፡
   ለ. በውስጡ በቂ የመድኃኒት መደርደሪያዎች፣ በማቀዝቀዣ የሚያዙ መድኃኒቶች ካሉ ማቀዝቀዣ ከነሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር፣ የግድግዳ ሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር ሊኖሩት ይገባል፡፡
   ሐ. ከፍተኛ ሙቀት ባሉባቸው አካባቢዎች መድኃኒቶች ያሉባቸውን ክፍሎች በሚያዳርስ ሁኔታ እንደሚሰራ የተረጋገጠ ኤር ኮንዲሽነር ወይም ቬንትሌተር ፣
   መ. የውጭ ጥገኛ፤ መርዛማና ተቀጣጣይ የሆኑ መድኃኒቶች ሊቀመጡበት የሚችል የተለየ ቦታ ሊኖሩት ይገባል፡፡
   ሠ. የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት መፀዳጃ ክፍል የውሃ አገልግሎትና የእጅ መታጠቢያ ሲንክ ያለው መሆን አለበት፡፡

## 8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

8.1 የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጠያቂው ወይም አመልካቹ ከመመሪያው ጋር በተያያዘው ቅጽ /ዕዝል አንድ/ መሠረት አግባብ ላለዉ አካል ወይም

አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ማመልከቻውን ሞልቶ ጥያቄውን ማቅረብ አለበት፡፡

8.2 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚጠይቅ ማንኛውም ተቋም ቅጹን ሞልቶ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከአስራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መልስ ማግኘት አለበት፣

8.3 አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ከሁለት እስከ ሶስት ባሉት የኮሚቴ አባላት ተቋሙን ኢንስፔክት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣

8.4 በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ሪፖርት መሠረት ኮሚቴው የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋሙ የተቀመጠዉን መሥፈርት ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ይሰጣል፣

8.5 በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ሪፖርት መሠረት መስፈርቶች ካልተሟሉ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋሙ ማሟላት ያለበትን ሁኔታዎች እንዲያሟላ በፅሑፍ ተነግሮት ካሟላ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ተደርጎ እንደገና በኢንስፔክተሮች ሊታይ ይችላል፡፡ ነገር ግን በተደጋጋሚ ከሁለት ጊዜ በላይ ታይቶለት ሳያሟላ ከቀረ ለመጨረሻ ጊዜ ከታየበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ በድጋሚ ይታይልኝ የሚል ጥያቄ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

8.6 የኮሚቴው ውሳኔ በሁሉም አባላት ተፈርሞና በቃለ-ጉባኤ ተይዞ በእያንዳንዱ አመልካች የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም ፋይል ውስጥ ተያያዞ መቀመጥ አለበት፣

8.7 አግባብ ያለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲሰጡ ወይም ሲያድሱ ወይም ምትክ ፈቃድ ሲሰጡ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የማሳወቂያ ቅጽ (እዝል ሦስት) መሠረት ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ማለትም የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣ ግብርና ቢሮ፣ የዞን፣ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች መላክ አለባቸው፡፡

# ክፍል አራት

# አጠቃላይ ድንጋጌዎች

## 9. የአገልግሎት ክፍያ

አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ፈቃድ ለማግኘት፣ ለማደስና ምትክ ፈቃድ ለመስጠት የሚደረገው ክፍያ በዕዝል 4 በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ይፈፀማል፡፡

## 10. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚታይበት ሥፍራ ስለማኖር

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም የተሰጠውን ዋናውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በተቋሙ መድኃኒት ማደያ ክፍል ውስጥ ሁልጊዜ ሊታይ በሚችልበት ቦታ ማንጠልጠል አለበት፡፡

## 11. የእንስሳት መድኃኒት ማሸጊያና ገላጭ ጽሁፍ

1. ማንኛውም ለሽያጭ የቀረበ የእንስሳት መድኃኒት በተገቢው ሁኔታ መታሸግ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ለሽያጭ የሚቀርብ የእንስሳት መድኃኒት ‘ለእንስሳት ሕክምና ጥቅም ብቻ የሚውል’ የሚል ገላጭ ፅሑፍ ሊኖረው ይገባል፡፡
3. ማንኛውም ለሽያጭ የሚቀርብ የእንስሳት መድኃኒት ማሸጊያ ላይ አያያዝና አጠ ቃቀሙን የሚገልፅ ገላጭ ፅሁፍ ሊኖረው ይገባል፡፡

## 12. መድኃኒት ግዥና ሽያጭ

1. በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ የተሰማራ ተቋም መድኃኒቶችን መግዛት የሚችለው የታደሰና ሕጋዊ ፍቃድ ካላቸው የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋዮች ብቻ ነው፡፡
2. ማንኛዉም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም ከሌላ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ካለ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም የእንስሳት መድኃኒትን መሸጥም ሆነ መግዛት አይችልም፡፡
3. በማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም ውስጥ የሚካሄድ የመድኃኒት ሽያጭ ወይም እደላ ተግባር የሚከናወነው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በተሰጠው ባለሙያ ኃላፊ ቁጥጥር ሥር ብቻ ይሆናል፡፡

4. ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜ አግባብ ባለው አካል ፈቃድ ተመሳሳይ የሙያ ፈቃድ ያለውና ውክልና በተሠጠው ወቅት ሌላ ሥራ የማይሠራ ባለሙያ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ተክቶ ሙሉ ጊዜ እንዲሰራ ማድረግ ይቻላል፡፡

5. በሽያጭ ወይም እደላ ወቅት በተፈጠረ ስህተት በተጠቃሚው ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ተጠያቂነቱን ኃላፊው ይወስዳል፡፡

6. በሽያጭ ወይም እደላ ወቅት ባለሙያው ለታካሚ እንስሳት ባለቤት ስለ መድኃኒቱ አጠቃቀምና ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ተገቢውን መረጃ በቃልና በጽሑፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 13. ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ደረሰኝ ለገዥው የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 14. የደንብ ልብስ

በማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋማት ውስጥ በእደላ ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ንጹህ ነጭ ኮት መልበስ ሲኖርበት ለመለያም እንዲያገለግለው በኮቱ የደረት ኪስ ላይ ስሙንና ሙያውን የሚያሳይ ባጅ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 15. የሥራ ሰዓት

የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም በሚገኝበት አካባቢ የሚኖረውን የሕዝብ ፍላጎት በማመዛዘነ እያንዳንዱ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም ክፍት ሆኖ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሰዓታት አግባብ ባለው አካል ይወሰናል፡፡

## 16. መድኃኒት አያያዝ

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም፣

1. መድኃኒቶችን እንደየባህሪያቸው በአግባቡ መያዝ፣
2. ማዘዣ ወረቀቶችና ሰነዶች ቁልፍ ባለው ቁምሳጥን ቆልፎ መያዝ፣
3. የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸው መጠበቅ ያለባቸው መድኃኒቶች በማቀዝቀዣ የመያዝና የሙቀተን ሁኔታ ቴርሞ ሜትር በመጠቀም መለካት ይኖርበታል፡፡

## 17. ሪከርድ አያያዝና ሪፖርት አደራረግ

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም፡

1. ስለመድኃኒቶች አከመቻቸት፣ አቀማመጣቸውና አስተዳደላቸውን የሚገልጹ ኢንቮይሶችን፣ ደረሰኞችንና የመሳሰሉትን ዝርዝር መረጃዎችን የመያዝ፤
2. መድኃኒት የታደለበት የሐኪም ማዘዣ ወረቀቶች በቀን፣ በወርና በዓመተ ምህረት በመለየት ለሁለት ዓመት በመድኃኒት ቤቱ ውስጥ የመያዝ፤
3. አግባብ ካለዉ አካል ወይም አግባብ ለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የሚደርሱትን መመሪያዎች በአግባቡ የመያዝ ሃላፊነት አለበት፡፡

## 18. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት

አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የተሰጠን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣

1. ከሐምሌ እሰከ ነሐሴ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም መታደስ አለበት፤
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምስክር ወረቀቱ ካልታደሰ በየወሩ 50 (ሃምሳ ብር) ተጨማሪ ቅጣት በመክፈል ለሚቀጥሉት 2 ወራት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይቻላል፤
3. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሳይታደስ ከቀረ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤
4. እድሳቱ የሚፈፀመው በዚህ መመሪያ መሠረት መመዘኛዎች የተጠበቁ ለመሆናቸው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት በሚቋቋመው ኮሚቴ ሲያረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

## 19. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ማንኛውም ተቋም ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት አመልካቹ የተበላሸው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንዲመለስ ካደረገ በኋላ ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
3. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ማንኛውም ተቋም ምትክ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሲጠይቅ አግባብ ካለው አካል ምስክር ወረቀቱ ስለመጥፋቱ በቂ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚጠይቅ ማንኛውም ተቋም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

## 20. ዝዉዉር ወይም የቦታ ለዉጥ

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም አግባብ ያለዉን አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ በማስፈቀድና አስፈላጊውን ክፍያና መስፈርት በማሟላት ከአንድ የስራ ቦታ ወደ ሌላ አዲስ የስራ ቦታ ተቋሙን ማዛወር ይችላል፡፡

## 21. የባለሙያ ለዉጥ

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም አግባብ ካለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ ፍቃድ ሳያገኝ የባለሙያ ለውጥ ማድረግ አይችልም፡፡

## 22. የተከለከሉ ተግባራት

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ተቋም፣

1. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም ክፍሎችን ለመኖሪያ፣ ለመኝታና ሌሎች ለመሳሰሉት ተጨማሪ ግልጋሎቶች ማዋል የለበትም፣
2. ከእንስሳት መድኃኒት ውጪ ሌሎች ማናቸውንም ዓይነት ዕቃዎች መሸጥ የለበትም፣
3. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱንም በእዳ መያዣነት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የለበትም፣
4. የእንስሳት መድኃኒት ከውጪ ማስመጣት፣ ወይም በጅምላ ማከፋፈል ወይም የሕክምና ሙያ ከሚፈቅደውና በማዘዣው ከተጠቀሰው መጠን አስበልጦ ወይም አሳንሶ ለተጠቃሚው ግለሰብ መሸጥ የለበትም፣
5. በእንስሳት ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ ብቻ የሚታደሉ መድኃኒቶችን ያለማዘዣ ወረቀት መሸጥ የለበትም፣
6. ሕጋዊና ወቅታዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሌለው ሰው ወይም ተቋም መግዛት ወይም በማንኛውም መንገድ መቀበል አይችልም፣
7. የመድኃኒት እደላ ተግባር ፈቃድ ከተሰጠው ወይም በአግባቡ ከተወከለው ባለሙያ ውጪ ማከናወን የለበትም፣
8. ደረጃው እንዲይዝ ከፈቀደለት የመድኃኒት ዝርዝር ውጪ መሸጥ ወይም በመደብሩ ይዞ መገኘት የለበትም፣

9. በእንስሳት መድኃኒት መደብርና የገጠር መድኃኒት ቤት የሚሰራ ማናቸውም ባለሙያ የመድኃኒት ዝግጅት ደባልቆ ለመቀመም ወይም ማናቸውንም መጠን ወይም የመድኃኒት ዝግጅት ወይም መርዝ ለማሰናዳት መሞከር የለበትም፣
10. ለሽያጭ የሚቀርቡ መድኃኒቶች መያዣ ላይ የተቋሙ ስምና አድራሻ ያለው ማህተም አድርጎ መሸጥ የለበትም፡፡

## 23. ግዴታ

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም በአካባቢው ተፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችን በተፈቀደላቸው መሠረት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ የተሰማራ ተቋም መድኃኒቶችን ህጋዊ ፈቃድ ካላቸው የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፍዮች ለመግዛትም ሆነ ገዝቶ ሲንቀሳቀስ አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዋናውን ወይም ኮፒውን ይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አምስት

# አስተዳደራዊ እርምጃዎች

## 24. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማገድ

በአዋጅ ቁጥር 728/2004 የተጠቀሱት የወንጀል ተጠያቂነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊታገድ ይችላል፡፡

1. ተቋሙን በኃላፊነት የሚመራው ባለሙያ በአእምሮ ሕመም ወይም ሌሎች ከሙያው ጋር የተያያዙ ችግሮች ወይም የአልኮል መጠጥ፣ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ሌላ ምጥን በመውሰድ በሚነሳ የአእምሮ መታወክ ምክንያት ወይም በዕድሜ መግፋት ምክንያት ተግባሩን ለማካሄድ ባለመቻሉ ለእንስሳት ጤና አደጋ የሚያመጣ ሆኖ ሲገኝ፣
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠባቸው መመዘኛዎች ሲጓደሉ፣
3. የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን ለመቆጣጠር ስልጣን የተሠጠው አካል ተግባሩን እንዳያከናውን እንቅፋት የፈጠረ ሲሆን፣
4. ተቋሙ አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ በንግድ ሥራ እንዳይሠማራ መታገዱ ሲረጋገጥ፣

5. ተቋሙ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓላማ ተቃራኒ ተግባር ሲፈጽም ከተገኘ፣
6. ሕጋዊና ወቅታዊ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ፍቃድ ከሌለው ሰው ወይም ተቋም መድኃኒት ሲገዛ ወይም ሲቀበል ከተገኘ፣
7. የመድኃኒት እደላ ተግባር ፍቃድ ከተሰጠው ወይም በአግባቡ ከተወከለው ባለሙያ ውጪ ንግዱ በሌላ ሰው ሲያከናውን ከተገኘ፣
8. የእንስሳት መድኃኒቶችን ለሌላ ችርቻሮ ተቋም በጅምላ ሲያከፋፍል የተገኘ እንደሆነ::

## 25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መሠረዝ

በአዋጅ ቁጥር 728/2004 የተጠቀሱት የወንጀል ተጠያቂነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከላይ በአንቀጽ 24 የተዘረዘሩትን ተግባራት ከሁለት ጊዜ በላይ መፈፀም እንዲሁም ከሚከተሉት መካከል በአንዱ ምክንያት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይችላል::

1. የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለሌላ ሰው ተላልፎ ከተገኘ፣
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው በማጭበርበር መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. ያልተመዘገበ ወይም የተከለሰ ወይም የተጭበረበረ ወይም በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባ ወይም አሳሳች ገላጭ ጽሁፍ የያዘ የእንስሳት መድኃኒት ይዞ ሲሸጥ ወይም ሲያከፋፍል ከተገኘ፣
4. የተበላሸ ወይም የአገልግሎት ዘመን ያለፈበት ወይም ገበያ ላይ እንዳይውል የታገደ መድኃኒት ሲሸጥ ወይም ሲያድል ከተገኘ፣
5. ሥራውን በራሱ ፈቃድ ሲያቋርጥ::

## 26. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ

1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ወይም ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን አግባብ ላለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ መመለስ አለበት፣
2. ሥራው ከተቋረጠ በኋላ በተቋሙ ውስጥ በክምችት የሚገኙ የእንስሳት መድኃኒቶችን አግባብ ባለዉ አካል ወይም አግባብ ባለዉ አካል የተወከለ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ተቋሙ አስፈላጊውን ሁሉ መፈፀም አለበት::

## 27. መመሪያዉን ስለማሻሻል

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት በማናቸውም ወቅት ይህን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

## 28. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች

1. "የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ሟሟላት ያለበት መመዘኛዎችና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ 2005" በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 29. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም

ጠርዙ ዳያ ደጋጋ (ዶ/ር)
የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

# ዕዝል

## ዕዝል አንድ

<u>የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅጽ</u>

1. የአመልካች ስም ከነአያት ______________________________

2. የአመልካች የመኖሪያ አድራሻ

   ክልል ______________________ ዞን ______________________

   ወረዳ ______________________ ከተማ ____________________

   ከፍተኛ _________________ቀበሌ ____________________

   የቤት ቁጥር __________________ስልክ ቁጥር ________________

3. ሊቋቋም የታሰበው የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ዓይነት

   3.1 የእንስሳት መድኃኒት መደብር

   3.2 የእንስሳት የገጠር መድኃኒት ቤት

4. የእንስሳት መድኃኒት የችርቻሮ ንግድ ድርጅቱ ባለቤትነት

   4.1 የግል

   4.2 ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

   4.3 የአክሲዮን /የውል መረጃ ይያያዝ/

5. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቱ ሊቋቋም የታሰበበት አድራሻ፣

   ክልል ______________________ ዞን ______________________

   ወረዳ ______________________ ከተማ ____________________

   ከፍተኛ _________________ቀበሌ ____________________

   የቤት ቁጥር __________________ስልክ ቁጥር ________________

6. አመልካች በእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቱ የሚኖራቸው ኃላፊነት፣

   6.1 ባለንብረት ☐

   6.2 ባለንብረትና ባለሙያ ☐

7. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቱን የሚመራው ባለሙያ

   7.1 ስም ከነአያት ______________________________________

   7.2 የሙያ ደረጃ ______________________________________

   7.3 በክልል አስፈፃሚ አካላት በባለሙያነት የተመዘገበበት ቁጥር ____________

8. ባለሙያው በዘርፉ ያሏቸው የሙያ ልምዶች መረጃ እንዲሁም ተቀጣሪ ከሆነ የውል ስምምነት ይያያዙ

9. የሚቋቋመው የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅት

   9.1 የውሃ አገልግሎት

   አለው ☐ የለውም ☐

9.2 የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት

አለው ☐ የለውም ☐

9.3 የስልክ አገልግሎት

አለው ☐ የለውም ☐

9.4 የፖስታ አገልግሎት

አለው ☐ የለውም ☐

9.5 አካባቢው ለእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ተግባር ተስማሚ

ነው ☐ አይደለም ☐

10. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቱ፣

10.1 የሚቋቋምበት አካባቢ

ቆላማ ☐ ደጋ ☐ ወይናደጋ ☐

10.2 የድርጅቱ ክፍሎች ጣራ ቁመት________ሜትር

10.3 የማደያ ክፍል ስፋት: ____ሜትር X ______ሜትር = ________ካሬ ሜትር

10.4 የማከማቻ ክፍል ስፋት: ____ሜትር X ______ሜትር =______ካሬ ሜትር

10.5 የማደያና የማከማቻ ክፍሎች በቂ መደርደሪያ

አላቸው ☐ የላቸውም ☐

10.6 የእንስሳት መድኃኒት ማደያ ባንኮኒ

አለው ☐ የለውም ☐

10.7 ማቀዝቀዣ ከነሙቀት መቆጣጠሪያው ቴርሞሜትር

አለው ☐ የለውም ☐

10.8 የእሳት አደጋ መከላከያ ማጥፊያ

አለው ☐ የለውም ☐

10.9 ለጽሕፈት ሥራ የሚጠቀምበት ጠረጴዛና ወንበሮች

አለው ☐ የለውም ☐

10.10 የልብስ መስቀያ

አለው ☐ የለውም ☐

10.11 መፀዳጃ ክፍል ከነውሃ አገልግሎቱና የእጅ መታጠቢያ ሲንክ

አለው ☐ የለውም ☐

10.12 ሌሎች ያሉት ዝግጅቶች በአባሪ ወረቀት ይዘርዘሩ::

10.13 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ጎርፍ የማያስገባ:

ነው ☐ አይደለም ☐

10.14 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅት የሚቋቋምበት ቤት ቆሻሻ የሌለበት አካባቢ: ነው ☐ አይደለም ☐

11. **እኔ ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸው መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ።**

**ስም** ______________________________

**ፊርማ** ______________________________

**ቀን** ______________________________

## ዕዝል ሁለት

<u>የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ ችርቻሮ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚጠይቁ ግለሰቦች ድርጅታዊ መመዘኛዎች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚሞላ የኢንስፔክሽን ቅጽ</u>

1. የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ ችርቻሮ ንግድ ድርጅቱ ስም

______________________________________________

2. የድርጅቱ አድራሻ

   ክልል ____________ ዞን ____________

   ከተማ ____________ ክፍተኛ ____________

   ወረዳ ____________ የቤት ቁጥር ____________

   የፖ.ሣ.ቁ. ____________ የስልክ ቁጥር ____________

3. የባለንብረቱ ሙሉ ስም ____________
4. የባለሙያው ሙሉ ስም ____________
5. የባለሙያ ምዝገባ ቁጥር ____________
6. የባለሙያው የሙያ ደረጃ ____________
7. የችርቻሮ ድርጅቱ ደረጃ

   7.1 የእንስሳት መድኃኒት መደብር ☐

   7.2 የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት ☐

8. ድርጅቱ

   8.1 የውሃ አገልግሎት

   አለው ☐ የለውም ☐

   8.2 የኤሌክትሪክ መብራት

   አለው ☐ የለውም ☐

   8.3 ማቀዝቀዣ ከነሙቀት መቆጣጠሪያው ቴርሞ ሜትር

   አለው ☐ የለውም ☐

   8.4 የስልክ አገልግሎት

   አለው ☐ የለውም ☐

   8.5 የፖስታ አገልግሎት

   አለው ☐ የለውም ☐

9. የድርጅቱ ዲዛይንና አሠራር

   9.1 የክፍሎቹ ወለል

   9.2 የክፍሎቹ ግድግዳ

   9.3 በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ያለው ነው ☐ አይደለም ☐

   9.4 የክፍሎቹ ጣራ ኮርኒስ

   ☐ ☐

አለው የለውም

9.5 የድርጅቱ አሠራር ከመሬት ከፍታ ኖሮት ጎርፍ የማያስገባ

ነው ☐ አይደለም ☐

10. የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቱ፣

10.1 የሚቋቋምበት አካባቢ

ቆላማ ☐ ደጋማ ☐ ወይናደጋ ☐

10.2 የድርጅቱ ክፍሎች ጣራ ቁመት ________ ሜትር ነው፡፡

10.3 የማደያ ክፍሉ ስፋት

_____________ ሜትር X ________ሜትር = __________ ካሬ ሜትር

10.4 የማከማቻ ክፍል ስፋት

_____________ሜትር X _________ሜትር = __________ ካሬ ሜትር

10.5 ማቀዝቀዣ ከነሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር

አለው ☐ የለውም ☐

10.6 የግድግዳ መቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር

አለው ☐ የለውም ☐

10.7 የእሳት አደጋ መከላከያ /ማጥፊያ/

አለው ☐ የለውም ☐

10.8 የጽሕፈት ሥራ የሚጠቀምበት ጠረጴዛና ወንበሮች

አለው ☐ የለውም ☐

10.9 ልብስ መስቀያ

አለው ☐ የለውም ☐

10.10 የመፀዳጃ ክፍል ከነውሃ አገልግሎት

አለው ☐ የለውም ☐

11. የድርጅቱ ውስጣዊ ይዘት፣

11.1 ወለሉ ጠንካራና ትክክል ነው ወይ? ____________________________________

11.2 ቤቱ ከልዩ ልዩ ነፍሳት የተጠበቀ ነው ወይ? ____________________________

11.3 መዝገያዎቹ በሙሉ ይሰራሉ ወይም አይሰሩም? __________________________

12. ስለድርጅቱ ሌሎች ያልተገለፁ ሁኔታዎች ካሉ ዝርዝር ሁኔታው ይገለጽ

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

13. ስሙ ከላይ የተጠቀሰው ድርጅት በ ____________________200_________ዓ.ም __ ____________ ሰዓት ተገኝተን አስፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ ድርጅቱን በሁሉም

ሁኔታ የተሟላ/ያልተሟላ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ስለዚህም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ እንደግፋለን/አንደግፍም፡፡

| የኢንስፔክተሮች ስም | የስራ ድርሻ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| ሀ.________________ | ____________ | ________ | ________ |
| ለ.________________ | ____________ | ________ | ________ |
| ሐ.________________ | ____________ | ________ | ________ |

14. የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የተዋቀረው ኮሚቴ ሰብሳቢ አስተያየት፣

ኢንስፔክተሮቹ የሰጡት አስተያየት ትክክል መሆኑን እያረጋገጥኩ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችል/የማይችል መሆኑን አስተያየቴን እገልፃለሁ፡፡

| ሙሉ ስም | ፊርማና | ቀን |
|---|---|---|
| ______________________ | ______________ | ____________ |

ዕዝል ሦስት

ቁጥር _____________

ቀን _________________

<u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲሰጥ ወይም ሲታደስ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ማሳወቂያ ቅፅ</u>

ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳዳርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

በ _______________________ክልል/መስተዳድር ዞን ____________ወረዳ ______________ ክ/ከተማ _________________ ቀበሌ ___________________ የቤት ቁ. ______________ ስ.ቁ. ____________________ ሞባይል _________________ ፖ.ሣ.ቁ. _______________ የሚገኝ ንብረትነቱ የአቶ/ወ/ሮ ________________________________________ የሆነውና በአቶ/ወ/ሮ/ዶ/ር ______________________________ የሙያ ደረጃ ___________________ የሙያ ምዝገባ ቁጥር ___________________ ባለሙያነት የሚመራው _______________ _________________________የተባለው የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት፣ የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ መደብር፣ በ__________ ቀን___________ወር __________ዓ.ም በተካሄደው ኢንስፔክሽን ተፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በመገኘቱ የብቃት ማረጋገጫ አዲስ/የታደሰለት/ምትክ ምስክር ወረቀት የተሰጠዉ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

ለክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ

ለክልሉ ግብርና ቢሮ/የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ

ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤት/ የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>

## ዕዝል አራት

### የአገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ዓይነት | አዲስ ፈቃድ ለማውጣት | እድሳት | ምትክ ፈቃድ | ለ2ኛ ዙር ቅድመ ፍቃድ ኢንስፔክሽን | ለ3ኛ ዙር ቅድመ ፍቃድ ኢንስፔክሽን | የባለ ሙያ ለውጥ | የቦታ ለውጥ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የእንስሳት መድኃኒት መደብር | 300 ብር | 150 ብር | 100 ብር | 300 ብር | 600 ብር | 150 ብር | 150 ብር |
| 2 | የእንስሳት ገጠር መድኃኒት ቤት | 200 ብር | 100 ብር | 100 ብር | 200 ብር | 400 ብር | 100 ብር | 100 ብር |